የምፅዓቱ መፅሐፍ ቅዱስ HOLY BIBLE የምሥራች

ቅጽ 85 ቁጥር 3(987)

“እርሱን የምትሹበት ዘመን ነውና በጽድቅ ዝሩ” (ሆሴዕ 10፡12)

ጌታ የሀገራችንን ሕልውና እንዲጠብቅ እንትጋ

(በሄንሪ ብላካቢ/ Henry Blackaby)

እግዚአብሔር ሕዝቦቹ ወደ እርሱ እንዲመለሱ እየተጣራ ነው። ወደ እግዚአብሔር የተቀደሰ ክብር መግባት እንድንችል አሰቀድመን ኃጢአታችንን ማወቅ አለብን። ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ግንኙነት እንዲኖረን የሚጠበቀው መንፈሳዊ መነቃቃትና ተሐድሶ ጋር የተያያዘ ነው። ሊፋጠን የሚገባው አንድ ትልቅ ጉዳይ ይጠብቀናል። ይህም ብርቱ ጉዳይ እግዚአብሔርን አወቅን የምንል ሁሉ ሀገራዊና አኅጉራዊ ከዚያም ዓለም አቀፋዊ ለሆነ ታላቅ የእግዚአብሔር ጉብኝት ራሳችንን በንሰሐ ማዘጋጀት ያሰፈልገናል።

በአሜሪካ በ1950ዎቹ አጋማሽ የነበረ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በእውነተኛ ልብ ሲያቀጣጥል አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ ሲያዳርስ አይተናል፣ ደግሞም አልፈንበታል። ያ መንፈሳዊ ልምምድ በበለጠ ሁኔታ ይመጣልናል።

እግዚአብሔር በእውነተኛ ልብ በተሰበረ መንፈስ ወደ እርሱ የሚጮኹትን እንደሚሰማ በቃሉ የተናገረው እውነትና ጊዜውን ጠብቆ የሚፈጸም ነው። “እግዚአብሔር ልቡ በእርሱ ዘንድ ፍጹም የሆነውን ያጸና ዘንድ ዐይኖቹ በምድር ሁሉ ይመለከታሉና” (2 ዜና መዋዕል 16፡9)።

ጌታ በቃሉ እንደተናገረው የቅኖች ጸሎት በእርሱ ዘንድ ፍሬ ያሰገኛል። “የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች” (ያዕቆብ 5፡16)።

የዚህ ሰዓት አጣዳፊ ተግባር

በዚህ ወቅት ጌታ የተናገራቸው የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች በታሪክ ከታዩት ሁሉ በግልጽ በሚታዩበትና በሚሰሙበት ጊዜ ትልቁ አጣዳፊ ሥራ የጌታን ፊት በንሰሐ መፈለግና ለራስና ለቤተሰብ፣ ለሀገርና ለዓለም ሀሉ በብርቱ መጸለይና መትጋት ነው። (2 ቆሮንቶስ 1፡20)

በእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል ሰለ መጸለይ

የምጽአቱ የምሰራች አገልግሎት ባልደረቦች ይህንን እትም የእግዚአብሔርን ፊት ሰለ መፈለግና በእርሱ ሰለ መታመን ለማቅረብ በመቻላችን ለጌታ ክብር እንሰጣለን።

በመጀመሪያው ገጽ ላይ እግዚአብሔር ሀገራችንን እንዲጠብቅ ሕዝቡ የእርሱን መንገድ በመፈለግ እንዲተጋ ወንድማችን ሄንሪ ብላካቢ የሰጠን መልእክት የወቅቱ ተገቢ መልእክት ነው።

እግዚአብሔር ጸሎትን ሰምቶ ለውጥና በረከትን የሚያመጣ ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። ይህ የጸሎት መልስ የእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል ነው። “በሰሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ” (2 ዜና መዋዕል 7፡14)።

“ለእናንተ የማሰባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም” (ትንቢተ ኤርምያስ 29፥11)።

እግዚአብሔር እንዴት ይቀርብናል

“ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፣ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል” የሚለው የትንቢት ቃል እያንዳንዱ ደቂቃ፣ ሰዓትና ቀን የጌታን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከሰባኪ፣ ከቤተሰብና ከተፈጥሮ ጭምር የምናገኝበት ወቅት ነው (ያዕቆብ 4፥8)።

እግዚአብሔር ወደ ሕዝቡ በሁሉም ጊዜ ሲቀርብ ኃይሉ፣ ብርታቱ፣ የሕይወት ማዳኑ፣ ድሉ፣ ፈውሱ፣ ጥበቃው፣ ብርሃኑ፣ እውነቱ፣ ማጽናናቱ፣ ጸጋና ምሕረቱ ይገኛሉ።

በሃገራችን “እግዚአብሔር የራቀው” የሚለው ብሂል ለክፉ ሰዎችና ለ ማይታዘዙ ሰዎች የተሰጠ መጠሪያ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ከማንም የማይርቅና ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ የሚቀበል ነውና ሁል ጊዜ እርሱን ከልባችን እንፈልገው፣ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ይቀርበናል፤ ሰላምና እረፍቱ በሕይወታችን ይበዛልናል (መጽሐፈ ነህምያ 1፥4፤ የሐዋርያት ሥራ 4፥24)።

የጸሎት ሰዎች ክፉውን ዓለም ይገለብጣሉ

(በኩዊንተን ኤቨረስት/Quinton J. Everset)

ዓለምን በሙሉ፣ ሃገራችንን እና እኛንም ጭምር የፈጠረ እውነተኛው አምላክ ዛሬ በብዙ ቦታዎች የተዘነጋና የተገፋ ነው።

እግዚአብሔርን ሕዝቡ የሚለየው በእግዚአብሔር ሕዝብ ምሳሌነት በብሉይ ዘመን የተገለጸው የእይሁድ ማኅበረሰብ ታሪክን በሚተርከው መልኩ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ የፈጠረውን ጌታ ባለመታዘዝ በረከቱ እንደ ተወሰደበትና ከእግዚአብሔር ቅጥር በራሱ ፍላጎት ወጥቶ መከራ፣ ሰደት፣ ግፍና ባርነት እንዳየው፣ በአዲሰ ኪዳንም ከዘርና ከጎሣ የ ተጠርቶ፣ በኢየሱሰ ክርስቶስ አምኖ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነው አዲሱ እሰራኤል እንዲሁ ከጌታ አሳብ እየወጣ ይገኛል።

ከእግዚአብሔር አሳብ መውጣት የአይሁድ ሕዝብ ወይም እሰራኤል የተባለው ብቻ ባሕርይ ሳይሆን፣ በሁሉም የዓለም ሕዝቦች ዘንድ የተከሰተ ጉድለት ነው።

ዛሬም እንደ ትናንቱ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲመለሰ ነቢያቱ ዳንኤል፣ ኤርምያስ፣ ኢሳይያስ፣ ወዘተ.፣ እንዲሁም ሐዋርያቱ ጴጥሮስ፣ ጳውሎስ፣ ፊልጶስ፣ ወዘተ. ያሉት ያሰፈልጉናል።

በየዘመናቱ ሰይጣን የሚያቀናብረውን አልቂትና ክፋት ከታሪክ እግዚአብሔር እየመከተ ድል የነሣውና የሚነሣው በሰሙ በሚያምኑት ቅዱሳን ብርቱ ጸሎትና ትጋት ነው።

ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ጸሎት ከግለሰብና ከቤተሰብ ይጀምራልና፣ ሁላችንም በግልና በቤተሰብ ወደ ጌታ እንመለስ፣ መንፈስ ቅዱስ በሚገልጠው ኃጢአታችንና ጉድለታችን ላይ ንሰሐ እንግባ (1ኛ ሳሙኤል 7፥5)።

“ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር ትጸልይልን ዘንድ አትታክት አሉት።” በተሐድሶ ዘመን በብርቱ ጸሎት የተደገፈ ለውጥ ለዓለም በጎ ነገሮች ሲያሰከትል፣ የከፋ እልቂት የተካሄደባቸው ሰፍራዎች የጸሎት ትጋት የጎደለባቸው ነበሩ። በሀገራችን ኢትዮጵያ የደርግ መንግሥት ማብቂያ ላይ የተካሄደው ብርቱ ሀገራዊ ጸሎት ሊመጣ ያለውን እልቂት እንዳሰቀረ ምሰክሮች ነን (የዮሐንሰ ወንጌል 15፡5፤ መዝሙረ ዳዊት 27፡1-7)።

የቤተ ክርስቲያን ትንቢታዊ ሚና

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያረጋግጠው፣ የትንቢት አገልግሎትና አገልጋዮቹ እስከ ጌታ ዳግም ምጽአት ድረስ ይኖራሉ፤ እንደ ቅዱስ ቃሉ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያነቃሉ፣ ለሚጠፋው ዓለም መልእክቱ እንዲደርስ ያደርጋሉ (ትንቢተ ኢሳይያስ 62፡6፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 12)። ፍቅርን ከእውነት ጋር ማለያየትና ማደባለቅ የተለመደ ስሕተት ነው። እውነት ያለ ፍቅር ሕጋዊ የሆነ ቢሆንም እንኳ፣ እውነት በሐሰት ሊቀየር አይገባም። ለሌሎች ያለን ፍቅር የተጠበቀ ቢሆንም፣ የምንፈራቸው ሰዎች ሲሰቱና ሲያስቱ በፍቅር ስም እውነቱን አለመግለጽና አለማረም በደል ነው። ነቢዩ ሕዝቅኤል ጠባቂዎች ያላቸው፣ ጌታም በጸሎት እንድንጠበቅ ያሳሰበን ሐሰተኞችን የመለየት ጉዳይ የተገባ ነው (ሰቆቃወ ኤርምያስ 2፥19፤ ማቴዎስ 26፥40)።

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ጌታ በዚህ አገልግሎት የሚሰይማቸው የእግዚአብሔር አገልጋዮች የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋትና ሐሰቱን ለመለየት እንጂ፣ ለምድራዊ ብልጽግና ሰዎችን ለማማለል አይደለም (ኤርምያስ 6፥12)።

የአገር ዳር ድንበር ጠባቂዎችና የመረጃ ሰዎች የሀገርና የመንግሥትን ሕልውና እንደሚጠብቁና አጥፊ ጠላትን እንደሚያስጠነቅቁና እንደሚያጋልጡ ሁሉ፣ የጌታ ቤት ነቢያትን፣ እረኞችና ሐዋርያት ሕዝቡን ከጥፋት የሚታደጉ አገልጋዮች ናቸው (ሕዝቅኤል 3፥17፤ ኢሳይያስ 62፥6)።

ለሀገራችን ሕልውና፣ ሉዓላዊነት፣ ሰላምና ብልጽግና በትጋት ለመቆም ክርስቲያኖች የበለጠ ክቡር ኃላፊነት፣ መብትና ግዴታ አለብን።

ሰዎች በፖለቲካ፣ በዘር፣ በሃይማኖት ቢለያዩም፣ አብረው በጋራ የሚኖሩባትን ሀገር መጠበቅ፣ መርዳት፣ መንከባከብና ለበጎ ሥራ ሁሉ ከመንግሥት ጋር መተባበር ይገባቸዋል።

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድ ነገድ አይሁድ ብቻ እስራኤል ተብሎ የተጠራ ሲሆን፣ በአዲስ ኪዳን ግን ከነገድ፣ ከቋንቋና ከዘር የተጠራና በመሲሑ ክርስቶስ የሚያምን ታላቅ ዘላለማዊ ሕዝብ ነው (1ኛ ተሰሎንቄ 5፥49፤ የዮሐንስ ራእይ 7፥19)።

የእማኞች ጸሎት ተሐድሶ ያመጣል፣ ዓለምን ይቀይራል

በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝብ ምሳሌ የነበረው የእይሁድ ማኅበረሰብ በጠላት ሲማረክ፣ ሲወረርና ሲጠቃ፣ የእግዚአብሔር አገልጋዮች፣ መሪዎች፣ ነቢያትና ነገሥታት ለጌታ ጸሎት እያቀረቡ እርነት ይገኝ ነበር (ትንቢተ ዳንኤል 9፥3፤ ዘጸአት 12፥13)።

ከግብፅ ባርነት በሙሴ መሪነት፣ ከባቢሎን ምርኮ በነቢያቱ በነህምያ፣ ዳንኤል፣ ኤርምያስ፣ ኢሳይያስና ሌሎቹ ጸሎት የእግዚአብሔር ሕዝብ ከገባበት ሥጋዊና መንፈሳዊ ባርነት ነጻ ወጥቷል።

በአዲስ ኪዳን መንፈሳዊና ሥጋዊ ጭቆና፣ በደል፣ ኃጢአትና ክፋትን የሚያሠራ ሰይጣንና ዓለምን የራሳችንንም ሥጋ ጭምር ፈተናና መከራ የምንወጣው በእግዚአብሔር ቅዱስ ዘላለማዊ የተሰፋ ቃል መሠረት ነው (ዮሐንስ 6፥51፤ ኤፌሶን 6፥12)።

በሰው ዘር ታሪክ ሁሉ በጎና ጠቃሚ ለውጦች አዋጆች መንግሥታትና ሕግጋት የ??? በእውነተኛ አማኞች ብርቱ ጸሎትና በእግዚአብሔር ቃል ምሪት የእግዚአብሔር ምሕረት እየፈሰሰላቸው መሆኑን የባርነትና ግፍ መቆም የቅኝ ገዢዎችም ወረራ ማብቃትና የፍትሕ መስተካከል ይመስክራሉ።

በእማኞች ጸሎት ምክንያት በብዙ ሀገሮች ሊመጣ የነበረ የእርስ በርስ እልቂት፣ ጥፋትና ረሀብ መወገዱን እናውቃለን። ዮሴፍ ወደ ግብፅ ምድር በወንድሞቹ ተሸጦ ሄዶ እግዚአብሔር ያከበረውና ለግብፅም ለራሱ ሕዝብ ለእይሁድም ታዳጊ የሆነው በሕልም ጸጋ ለእግዚአብሔር ጸሎቱንና መሻቱን በማቅረብ ነበር።

በተሐድሶ ዘመን መገባደጃ ላይ በፈረንሳይ በተነሣው አብዮት የፓሪስ ኮሚኒየን የተባሉ የኮሚንስቶች መዋቅር ቢፈጠርም፣ የነገሥታቱ ሄራ ብዙ የእርስ በርስ እልቂት ሲከናወን፣ በጀርመንና በስካንድኔቪያ ሀገሮች ግን በብርቱ ጸሎት የተካሄደው ተሐድሶ ለሕዝባቸው ሰላም በማስገኘት እልቂትን አስቀርቷል።

በቅዱስ መጽሐፍ እንደተጻፈው፣ እግዚአብሔር ለሰው ፊት ያማያዳላ ነጭ፣ ጥቁር፣ ይሁዲ፣ አሕዛብ የማይል፤ በዘርና በጎሣ የማይለያይ ነውና፣ በብርቱ ጸሎት ለሀገራችን እንድረስላት (ሐዋርያት ሥራ 10፥34)።

መንፈሳዊ መነቃቃት፣ ተሐድሶና ክብር መገለጥ

በቴድ ሬንድል/Ted S Rendail

“ይመለሳሉ፤ ይታደሳሉ” (ሆሴዕ 14፥7)።

በትንቢተ ሆሴዕ የተገለጠውና በትንቢተ ኢሳይያስም “በመመለስና በማረፍ ይድናሉ” ተብሎ የተገለጸላቸው ከእግዚአብሔር አሳብና ዕቅድ ውጭ ከሚጠበቅባቸው መንፈሳዊ ደረጃ ለወረዱ፣ ለተሰናከሉና ለሳቱ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ነው።

ነቢዩ ሆሴዕ ባገለገለበት ዘመን በእሰራኤል አሥር ነገዶች/ጎሣዎች ሲገኙ፣ ትልቁ የኤፍሬም ነገድ /ጎሣ/ ወገን ነበር። ኤፍሬም የሚለው ቃል ትርጉሙ ፍሬያማ የሚል በመሆኑ፣ ነቢዩ አገልግሎቱ ፍሬያማ እንዲሆን በዚህ ላይ ያተኩራል። “ኤፍሬም ተመታ፥ ሥሩም ደረቀ፥ ፍሬም አያፈራም” (ሆሴዕ 9፥16)።

ፍሬያማ ሰለ መሆን በሚገባ ልናሰብበት ያስፈልጋል። እምነት፣ አገልግሎት፣ ሕይወትና ማንኛውም መስተጋብር የሚለካው በፍሬው ሲሆን፣ የእግዚአብሔር የሆኑ አገልጋዮችም ሆኑ ሕዝቦቹ የሚለዩት በፍሬያቸው መሆኑን ጌታ ያስተምረናል። “...ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ” (ማቴዎስ 7፥ 15)።

የማንኛውም እምነትና መንፈሳዊ አገልግሎት መነቃቃትና መታደስ መለኪያው ፍሬው በመሆኑ፣ በፍሬ ላይ ማተኮር እጅግ ያስፈልጋል።

ለመንፈሳዊ መነቃቃትና ተሐድሶ ወይም ለማንኛውም እንቅስቃሴ ፍሬያችን ያማረና እንደ እግዚአብሔር አሳብ እንዲሆን ማቀድ፣ ማስብ፣ መጸለይና መሰማራት አለብን። “ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ” (ሆሴዕ 14፥1)። ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ተቀዳሚው ነገር በሕይወታችን ያለውን በቅዱስ ቃሉና በቅዱስ መንፈሱ የሚገለጠውን እርምና ኃጢአት መናዘዝና በጌታ እርዳታ ማስወገድ ነው (ሆሴዕ 14፥2)።

የመንፈሳዊ መነቃቃት/ተሐድሶ መነሻ

በእግዚአብሔር ቤትና መንግሥት ውስጥ መንፈሳዊ መነቃቃትና ተሐድሶ መነሻ ራሱ እግዚአብሔር የሚልከው ቅዱስ መንፈሱ የሰዎች ልብ ተነክቶ በንስሐ መመለሱ ላይ ነው (ሆሴዕ 14፥4)።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የታዩት ተሐድሶዎችና መንፈሳዊ መነቃቃቶች ሁሉ የተካሄዱት መንፈሳዊ ጽልመትና የሞራል ውድቀት በስፈነባቸው ወቅቶች ነበር፤ አሁንም ነው፤ ወደ ፊትም ይሆናል። ስለዚህ፣ አሁን ባለንበት ሁኔታም ጌታ እንደሚሠራ ሁልጊዜም ያው መሆኑን በቃሉ ታምነን ኃጢአታችንን በመናዘዝ ለመንፈሳዊ ተሐድሶና መነቃቃት እንነሣ (ወደ ዕብራውያን 13፥8)።

የየዕለቱ የእምነት ጉዞ (በጄምስ ማኮንኪ/James H. McConkey)

እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ፣ አማኞች በራሳቸው መታመንን አሰወግደው በእግዚአብሔር ላይ እንዲታመኑ ቅዱስ ቃሉ ያስተምራል። “በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ” (መጽሐፈ ምሳሌ 3፥5)።

እግዚአብሔርን የምንታመነው እርሱ ሁሉንም መልካም ነገር ለእኛ ማድረግ የሚችል ሁሉን ቻይ አምላክ መሆኑን በመቀበል ሲሆን፣ እርሱ በሰጠን ማንነት ላይ ግን እምነት በማጣት ራሳችንን መጣል የለብንም። በአሮጌ ሕይወታችን ሁሉንም ነገር በራሳችን ጥበብና ችሎታ እንፈጽማለን ብለን የምናስብ ሲሆን፣ በክርስቶስ ካመንን ግን ሁሉን በሚያስችል በክርስቶስ በእግዚአብሔር እንታመናለን፣ እንኖራለንም (ፊልጵስዮስ 4፥13)።

እውነተኛው እምነት በሕይወታችን እንዲገኝ ክርስቶስን መስለን ልንኖር ያሻል። ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ውጭ ሰዎች በዘርና በቋንቋ እንደሚለያዩ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ደራሲዎች ዘንድ የታወቀ ሲሆን፣ ይህን ብልሽት ለማሰወገድ እንደ ቃሉ ለሚያስተምሩ፣ ሙያዊ አስተያየት ለሚሰጡና በአእምሮ ለሚያበረታቱ አገልጋዮች ምስጋና ልናቀርብ እንወዳለን (ዮሐንስ ወንጌል 4፥34)።

የጌታ እምነት በየጊዜው የሚላክልን ኃይልና ጥበቃ ባለቤት ወገናችንና ለዓለም የማይታወቅ ዘላለማዊ ምግብ ሆኗል። እምነት ከመሰማት ነው፤ መሰማትም በእግዚአብሔር ቃል የታዘዘ የምንድንበት ኃላፊነታችን፣ ግዴታችንና ጥቅማችን ነው (ሮሜ 10፥17)።

የእግዚአብሔር ፈቃድ እንቅስቃሴ

በማንኛውም የእግዚአብሔር ሥራ በመላው ዓለም በቀዳሚዎቹ የክርስተና መጀመሪያ ሀገሮች መካከል አንዷ በሆነችው ኢትዮጵያ ላለን የጌታ ምሕረት እንደ ቀጠለልን የምናረጋግጠው በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈና ለሚያምኑ ሁሉ የተሰጠ ነው (ወደ ዕብራውያን 11)።

በዘመናችን የጸጋ ተጓዥነት የሚታወቀው ሰዎች በእምነት ተሞልተው የእምነት እንቅስቃሴ በማድረግ የሚኖሩበት ሲሆን ነው።

የእግዘአብሔር ሰጦታዎች እንደ ሌሎቹ ሰጦታዎች ለተገቢ ዓላማ መዋል ሲገባቸው በዓለም ሰዎች ምድራዊ አሠራር ልዩነቱ ሕዝቦችን ለመበዝበዝ ሲጠቀሙበት ያሳዝናልና ከዚህ እንራቅ (ወደ ዕብራውያን 12)።

የእምነት ጉዟችን በሚገባ እንዲፈጸም የክርስቶስን የሕይወት ልምምዶች መከተል ይገባናል።

ጸምና ጸሎት - የማይነጣጠሉ የእግዚአብሔር ሥራ ማሰፈጸሚያዎች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ክፉውን መንፈስ ለምን እንዳላስወጡ በመግለጽ፣ በአገልግሎት መቀጠል እንዳለብን በቃሉ አስተምሮናል።

የአማኞች እምነት ሕያው ሆኖ ለመጭው ትወልድ የሚደርሰው በብርቱ ጸሎት፣ ዜማና መሰደድ ውስጥ ነው (ሐዋርያት 16፥25፤ ወደ ዕብራውያን 11፥6)።

እምነትና ጸሎት ይፈልጋል

የእግዚአብሔርን ቤት ሥራ በእምነት ለመፈጸም ጸሎት ተፈላጊ ጉዳይ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእምነት ያልተካሄዱ ጸሎቶች የእግዚአብሔርን ምላሾች እንደማያስከትሉ

አስተምሯል (ማርቆስ 11፥12፣ ማቴዎስ 17፥19)።

የእግዚአብሔርን ቤት አገልግሎት ለመወጣት ዳገቱን መውጣትና አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ማለፍን ይጠይቃል። ክርስትና በሂደቱና በእውነተኛ መልኩ ፈተናዎችን በማለፍና ጨለማን በመግፈፍ ዘላለማዊ ሕይወት ያቀዳጃል።

ጸሎት እምነትን ይጠይቃል

ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ ጸሎቶች ሁሉ መልስ የሚያገኙት በእምነት ሲካሄዱ ነው። ከጌታችን ጋር በጾምና በጸሎት የምናሳልፈው ጊዜ ሁሉ፣ በእምነት የምንጠይቃቸው የጸሎት ርእሶች ሁሉ መልስ እንዲያገኙ መፈጸም ይኖርባቸዋል። በጌታ ፈቃድ መልስም ይዘገያል፤ ይህም ለበጎ ነው። በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ፣ በጾም ደግሞ የማይታዩ የጸሎት ጥያቄዎች መስናክሎችና ግድግዳዎች ይወገዳሉ። የሰማይ መስኮቶች ይከፈታሉ። ጌታ፣ “እምነት ቢኖራችሁ፣ አንዳች የሚሳናችሁ ነገር የለም” ብሎ ያስተማረን ያለማመናችን እንዲወገድና በጌታችን ላይ ሙሉ በሙሉ በመተማመን በጸሎት እንድንተጋ ለማሳሰብ ነውና፣ በእምነት በጾምና በጸሎት እንትጋ (የማቴዎስ ወንጌል 17፥19)።

በእምነት ማደግና የእምነትን መስናክል ሰለ ማሰወገድ

George D. Watson/በጆርጅ ዋትሰን

እምነት የመንፈሳዊ ሕይወታችን ሁሉ ገላጭና ወሳኝ የእግዚአብሔር ልዩ ሰጦታ ነው። እምነት የሚያድግ የሚሰፋፋ የሆነውን ያህል፣ በኃጢአትና በቅዱስ ቃሉ በመለየት የሚጠፋ ሲሆን፣ በጸሎትና በንሰሐ ሕይወት የሚለመልም ነው (ማቴዎስ 17፥ 20፤ ወደ ዕብራውያን 3፥12)።

የጸሎታችን መልስ መዘግየት፣ በየአካባቢያችን የምናየው የእምነት መጥፋትና የትምህርት ሰሕተት በእምነታችን ላይ ተጽዕኖ ቢያሳድሩም፣ እንደ እግዚአብሔር የተሰፋ ቃል በመጽናናት እምነታችንን በቅዱስ መንፈሱ በመጠበቅ ሕይወታችን እየጠራ የእግዚአብሔር ክብር መግለጫ ይሆናል (ማቴዎስ 24፥ 30)።

እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ የራሱ ሕዝብ ለመሆኑ ምሳሌ የሆነው የእይሁድ ማኅበረሰብ እንዳይጠፉ በበረሃ በሐሩሩ ሳሉ የላከላቸው የሚያድንና የሚያረሰርስ ውኃ በአዲስ ኪዳን በልጁ በክርስቶስ ላመኑት ሕዝቦቹ ሁሉ የፈሰሰውን መንፈስ ቅዱስን አመልካች ነው (ኦሪት ዘኁልቁ 21፥16፤ የሐዋርያት ሥራ 2፥2)።

እንዲህ ነፍስና ሥጋን የሚባርከው እንዳይመጣ መስናክል የሆነው ትልቁ እንቅፋት የመንፈስ ቅዱስን ሥራ መቃወም፣ መሳደብና በኃጢአት ከጌታ መለየት ነውና፣ እንመለስ (ማቴዎስ 12፥31፤ ኤፌሶን 4፥30)።

የእግዚአብሔር ሰዎች ዓይኖቻቸውን ከእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል ላይ በማንሣት በዙሪያቸውና በዓለም ባሉት ነገሮች ከተወሰዱ፣ ያ ኃያል የሆነው ተራራውን ነቅሎ የሚጥል እምነታቸው ይጠፋል (ማቴዎስ 14፥31)።

የእምነት ሰዎች እንዲበረታቱ እርስ በርሳቸው የእምነትን መልካም ጉዳዮች መነጋገርና በእምነት ሩጫቸው መገሰገስ ይገባቸዋል። በዚያን ጊዜ ጽኑ፣ ኃያልና የዓለምን እንቆቅልሽ-ፈቺ ይሆናሉ (ወደ ዕብራውያን 12)።

ኃጢአት በትንሽ ቀዳዳ ወደ ሕይወታችን እንዳይገባ እምነትን የሚያጎድል ማናቸውንም አሳብ፣ ወሬ፣ ፖለቲካ፣ ፍልስፍናና ሚዲያ ከሕይወታችን በማራቅ፣ በየጊዜው የሚያድሰውን የእግዚአብሔር ቃል በመመገብ አእምሯችንና አስተሳሰባችን በመለወጥ የእግዚአብሔር ውክልናችን ለሰው ሁሉ ይታወቅ (ወደ ሮሜ ሰዎች 12፥2)። “እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ…ናችሁ” (1ኛ ጴጥሮስ 2፥9)።

የኢትዮጵያ የእምነት ሂደቶችና ተግዳሮቶች

(በቄስ ቻፕሊያን ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ)

“ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች” (መዝሙረ ዳዊት 67፥39)።

ስለ ሃገራችን ኢትዮጵያ የምንመሰክረው፣ የምናምነውና የምንኖረው በሕያው የእግዚአብሔር ቃል እንደተጻፈው ነው። በሕይወታችን ከልጅነት ጊዜ ጀምሮ እጆችንን ወደምንታመንበት ሰው ስንዘረጋ የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደምናገኝ የታወቀ ነው። ስለዚህ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በሁሉ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር በቅን ልብና በእውነተኛ መንፈስ እጆችንን ልንዘረጋ ያስፈልገናል።

እኛ ኢትዮጵያውያን እውነተኛው ወንጌል በሶርያውያን የእግዚአብሔር መልእክተኞች በእነፍሬምናጦስ (ኣባ ሰላማ) አማካይነት ከደረሰን ወቅት ጀምሮ እጆችንን ለእግዚአብሔር የመዘርጋቱ ዕድልና ጥቅም አለን። የእግዚአብሔር ብቸኛ ወኪልና ልጅ አምላክና ሰው በሆነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለእግዚአብሔር እጆችንን የመዘርጋት ዕድሉና መብቱ አለን (የዮሐንስ ወንጌል 14፥6)።

አይሁድ እግዚአብሔር ለራሱ ሕዝብነት ምሳሌ ያደረጋቸው ራሱን የዓለምን መድኃኒትና ጌታ ክርስቶስን እንዳልተቀበሉት እንዳንሆን ይህን ለሁሉ እናሳስብ፣ እንከተል (ዮሐንስ 1፥12)።

ከብሉይ ዘመን ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ያታወቀች የሀገራችን ኢትዮጵያ ሕዝቦች እምነት እንዲበረታታ፣ እንዲያድግና በእውነት ላይ እንዲጸና ይህ እውነት የገባን ሁሉ ልንተጋና ልንጋደል ያስፈልጋል።

የእውነተኛው የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነቢያቱ፣ ሐዋርያቱና የጥንት ዘመን ክርስቲያኖች የገጠማቸው መከራና ሥቃይ በሁሉም እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮች ላይ ሊደርስ የግድ ነው (2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡12፤ ወደ ዕብራውያን 11፥34)።

የሰላምና የፍቅር መሠረትና ሰጭ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ሁሉ እንደሚወድና እንደሚያድን የተነገረው ሁለንተናዊ የወንጌል የምሰራች ቃል ኢትዮጵያን እንደሚያካትት እምነን ያመነውን ይህንን ሀቅ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ እንመሰክር፣ እንናገር፣ እናድርስ (ዮሐንስ 1፥12፤ የዮሐንስ ወንጌል 3፥16) ። “እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ” (የሐዋርያት ሥራ 1፥8)። ኢትዮጵያውያን ሁሉ የክርስቶስ ምስክሮች እንሁን፤ እንቀበለው።

ዓለም አቀፍ ምስክርነቶች

ከናይጄሪያ

ሃሌሉያ ከናይጄሪያ! በየጊዜው የምትልኩልኝ የምጽአቱ የምሰራች ልቤንና መንፈሴን እየለወጠ ከለዘብታ ሕይወት ለክርስቶስ የምመሰክር አድርጎኛል። ለዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ ይክበር፤ እናንተም አብዝቶ በእጥፉ ይባርካችሁ!

ከደቡብ ኮርያ

ድሮ ከምኖርበት የደቡብ ኮርያ ወደ ሌላ ሰፍራ ከመጣሁ ጀምሮ የነበረኝ ልምምድ እየጠፋብኝ በሄደበት ወቅት ለደረሰልኝ የምጽአቱ የምሰራች ጌታ የተመሰገነ ይሁን። ይህንን ሕይወት-ሰጭ ጋዜጣ ለራሴና ለሌሎች መንፈሳዊ ሕይወት ትልቅ ድጋፍ-ሰጭ ነውና መላካችሁን ቀጥሉ።

ከፓፑዋ ኒው ጊኒ

የሐምሌና የነሐሴ 2017 ዓ.ም እትም ከደረሰኝ ጀምሮ የምጽአቱ የምሰራች ጋዜጣ ለሕይወቴ ትልቅ አንቀሳቃሽ ሆኖልኛል። ይህንን ፍሬያማ ያደረገኝን ጋዜጣችሁን ያሰጀመራችሁ ጌታ የተመሰገነ ይሁን። ለአገልግሎታችሁ በጸሎት

እተባበራለሁ፤ በሚቀጥለው ወር ለአገልግሎቱ የሚቻለኝን በፖስታ ቤት በኩል እልካለሁ።

ከኒውዚላንድ

ወላጅ እናቴ በሚቀጥለው ሳምንት 94 ዓመቷን ትይዛለች። በዚህ ሁሉ ዘመኗ እናቴ የምጽአቱ የምሰራችን መከታተል የሰጣትን ጥቅሞች ለእኛ ለልጆቿና ለልጅ ልጆቿ እየመሰከረችልን ትልቅ የበረከት ምንጭ ሆናልናለች። ጌታ እግዚአብሔር ይህን መልካም ሥራችሁን ይባርክ!

ከእንግሊዝ

የምጽአቱ የምሰራችን መከታተል የጀመርኩት በማረሚያ ቤት ከታሰርኩበት ጊዜ ጀምሮ ነው። የምጽአቱ የምሰራችን ካገኘሁ ጀምሮ የትክክለኛ ክርስትና ትርጉምን በማግኘት፣ ለሌሎች በማካፈል በእምነት በመገሰገሰ ላይ ነኝ። ጌታ ሰለዚህ ድንቅ ሰጦታው የተመሰገነ ይሁን፤ አሜን!

የጸሎት ርእሶችና ማሰታወቂያዎች

በኢራን ሰለሚደረግ የሳተላይት አገልግሎት

ለእግዚአብሔር ሕዝብ ተብሎ በብሉይ ኪዳን ለሚታወቀው አይሁድ ትልቅ ድጋፍ ያደርጉና ከእልቂት የታደጉት የቀድሞ ፋርሶች፣ የአሁኗ ኢራን፣ ሕዝቦችን በጸሎት እናሰባቸው። ቲፒት አገልግሎት በሳተላይት ለኢራን የሚያሰተላልፈውን የወንጌል ፕሮግራም በጸሎትና በሚቻለን ሁሉ እንደግፍ፤ እንመሰክር።

የሕጻናት ጋብቻ በፓኪሰታን ታገደ

በብዙ ሀገሮች ሕፃናትን ለጋብቻና ለወሲብ የሚዳርጉ ክፉ ልማዶች በመወገድ ላይ ናቸው። ከዚህ ዓመት ጀምሮ በፓኪሰታን ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ሴቶች ላይ ይደረጉ የነበሩ ጋብቻዎች በአዋጅ ታግደዋል። በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች ሀገሮች ሕፃናትን ለጋብቻ፣ ለወሲብና ለጉልበት ሥራ የሚያሠቃዩትን ጌታ እንዲገታ በጸሎት እንትጋ፤ ድምፃችንንም በያለንበት እናሰማ።

ላልዳኑት ሁሉ እንጸልይ

በመላው ዓለም፣ በሀገራችን ኢትዮጵያም ጭምር፣ ከገሀነምና ለሰይጣንና ለመላእክቱ ከተዘጋጀው ቅጣት ይድኑ ዘንድ ክርሰቶስን የማያውቁት ሁሉ እንዲያውቁት እንጸልይ።

ማሳሰቢያ ከአሰተባባሪው

ይህ የምጽአቱ የምሰራች መንፈሳዊ ጋዜጣ አማርኛን ለሚያውቁ መንፈሳዊ ድጋፍ ለመሰጠት በበጎ ፈቃድ የሚካሄድ አገልግሎት ነው። ሳትመቱን ለመቀጠልና ብዙዎችን ለመድረስ እንድንችል በጸሎትና በሚቻላችሁ የገንዘብ እርዳታ ትብብራችሁ ይድረሰን።

ቄስ ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ/ አሰተባባሪ

የመዳን ምክሮች

1. ኃጢአተኛ ሰለ መሆናችን የጌታ ቃልና ምሰክሮች ሲነግሩን ቃሉን ሰምተን በንሰሐ እንመለሰ (ዮሐንሰ 3፡16፤ ሮሜ 3፡23፤ 6፡23)።
2. ክርሰቶስ እንደ ሞተልንና እንደ ተነሣ፣ ዳግመኛም እንደሚመለስ እንመን። ወደሚቀርበን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ወደሚያምን ማሳበር እንቀላቀል።

የምጽአቱ የምሰራች አገልግሎት
Amharic Herald of His Coming
የፖ.ሣ.ቁ /P.O.Box/ 8986
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia
ሰርጭት፦ ብርሃኑ ጥርሰማ
ሰልክ፦ 0993154034
አርታ ፦ ዘነበ ገብረሐና
ታይፕና ዲዛይን፦ አቤኔዘር ጽሕፈት ሥራ፤ መካኒሳ በሳሚ ማተሚያ ታተመ።

በነጻ የሚሰራጭ